


በፕሬዘደንት
ቶማስ ኤስ ሞንሰን

# ለአገልግሎት የሚጠራው የአዳኝ ጥሪ

ሂሳብ ያጠኑት ሁሉ አካፋው ምን እንደሆነ ያውቃሉ። ለኋላኛው ቀን ቅዱሳን፣ አንድ ላይ የሚያስተሳስረን የጋራ አፋይ አለ። ያም የጋራ አካፋይም በምድር ላይ ባለችው የእግዚአብሔር መንግስት እያንዳንዳችን እንድናሟላ የተቀበልነው ጥሪ ነው።

ጥሪው ወደ እናንተ ሲመጣ በማጉረምረም ጥፋተኛ ናችሁ? ወይም የሰማይ አባስ የሚጠራቸውን እንደሚባርክ በማወቅ፣ ወንድሞቻችሁን እና እህቶቻችሁን ለማገልገል የሚሰጣችሁን እያንዳንዱን እድል በምስጋና ትቀበላላችሁ?

የማገልገል የውድ እድላችንን እውነተኛ አላማ እንዳይጠፋብን ተስፋ አለኝ። ያም አላማ፣ ዘለአለማዊው አላማ፣ ጌታ የተናገረው እና በየታላቅ ዋጋ ዕንቁ ውስጥ የሚገኘው ነው፥ “እነሆ፣ የሰውን ህያውነት እና ዘለአለማዊ ህይወት ማምጣት ስራዬ እና ክብሬ ይህ ነው።”[1]

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባልነት እራስን የማመቻቸት ሽፋን ሳይሆን የሀላፊነት ካባ እንደሆነ ሁልጊዜም እናስታውስ። እራሳችንን ከማዳን በተጨማሪ፣ ሀላፊነታችን ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር ሰለስቲያል መንግስት ለመምራት ነው።

እግዚአብሔርን ማገልገያ መንገድ ላይ ለመራመድ ፈቃደኛ በመሆን፣ ሼክስፒር ስለጻፈበት ካርዲናል ዎዝሊ በምንም አንሆንም። ንጉሱን ለማገልገል ያለው ሀይል በሙሉ ተወስዶበት፣ እንዲህ በሀዘን አለቀሰ፥

*ንጉሱን ባገለገልኩ አይነት አምላኬን በግማሽ ቅንአት ባገለግል*
*በእዚህ እድሜዬ*
*ለጠላቶቼ በእራቁቴ አይተወኝም ነበር።*[2]

ሰማይ ምን አይነት አገልግሎች ትፈልጋለች? “ጌታ ልብን እና ፍላጎት ያለውን አዕምሮ ይፈልጋል፤ እናም ፍላጎት ያለው እና ታዛዡም በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት የፅዮን ምድርን በረከት ይበላሉ።”[3]

የፕሬዘደንት ጆን ቴይለርን (1808–87) ቃላት ሳስብባቸው ነገሮችን እንዳሰላስል ያደርጉኛል፥ “ጥሪያችሁን ካላጎላችሁ፣ ሀላፊነታችሁን ብታከናውኑ ልታድኑ ለምትችሉት እግዚአብሔር ሀላፊ ያደርጋችኋል።”[4]

በሰዎች መካከል ሲያገለግል የነበረው የኢየሱስ ህይወት በሀይል እንደሚያበራ ብርሀን አይነት ነው። ኢየሱስ ሽባ ለሆኑት ሰዎች እጆችና እግሮች ጥንካሬ፣ ለአይነ ስውር ሰዎች አይኖች ብርሀን፣ ለደንቆሮዎች ጆሮ ድምጽ፣ እና ለሞተው ሰውነት ትንፋስ ሲያመጣ “እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ”[5] በማለት አውጇል።

በመልካሙ ሰማራዊ ምሳሌ፣ መምህር ጎረቤታችንን እንደ እራሳችን እንድንወድ አስተምሮናል።[6] ለሀብታሙ ወጣት ገዢ በሰጠው መልስም፣ ራስ ወዳጅነታችንን እንድንጥል አስተምሯል።[7] 5 ሺሆችን በመመገብ፣ የሌሎች ፍላጎቶችን እንድናሟላ አስተምሮናል።[8] እናም በተራራ ስበካው፣ የእግዚአብሔር መንግስትን በመጀመሪያ እንድንፈልግ አስተምሮናል።[9]

በአዲሷ አለምም፣ ከሞት የተነሳው ጌታ "እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ ይህ የእኔ ወንጌል ነው፤ እናም በቤተክርስቲያኔም መስራት ያለባችሁንም ነገሮች ታውቃላችሁና፤ እኔ ስሰራው ያያችሁትን ስራ እናንተም ደግሞ ስሩ፤ ምክንያቱም ስሰራ ያያችሁትን ስራ እናንተም ስሩ።"[10]

እኛም "የናዝሬቱን ኢየሱስን . . . መልካም እያደረገ . . . [በዞረበት]" ጥላ ውስጥ ስናገለግል፣ ሌሎችን እንባርካለን።[11] ልጆቹን በማገልገል የሰማይ አባታችንን ስናገለግል እግዚአብሔር ደስታን እንድናገኝ ይባርከናል።

ማስታወሻዎች

1. ሙሴ 1፥39
2. ዊልያም ሼክስፒር፣ *King Henry the Eighth, act* 3፣ scene 2፣ ቁጥሮች 456–58።
3. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 64፥34
4. *Teachings of Presidents of the Church: John Taylor* (2001)፣ 164።
5. ሉቃስ 22፥27
6. ሉቃስ 10፥30–37 ተመልከቱ፣ ደግሞም ማቴዎስ 22፥39 ተመልከቱ።
7. ማቴዎስ 19፥16–24፣ ማርቆስ 10፥17–25፤ ሉቃስ 18፥18–25 ተመልከቱ።
8. ማቴዎስ 14፥15–21፤ ማርቆስ 6፥31–44፤ ሉቃስ 9፥10–17፤ ዮሀንስ 6፥5–13 ተመልከቱ።
9. ማቴዎስ 6፥33 ተመልከቱ
10. 3 ኔፊ 27፥21።
11. የሐዋሪያት ስራ 10፥38።

### ከዚህ መልእክት ማስተማር።

"[ጌታ] ሀላፊነታችንን ካከናወንን እንድንወድቅ አይፈቅድም። ከመጋቢነታችን እና ከችሎታችን በላይ እንድንጎላ ያደርገናል። . . . ለሰው ዘር ከሚመቱት አስደሳች አጋጣሚዎች ይህ አንዱ ነው" (Ezra Taft Benson፣ in *Teaching፣ No Greater Call* [1999]፣ 20)። ጌታ የእናንተን ወይም የምታውቁትን ሰው ችሎታ ሲያጎላ የነበረውን አጋጣሚ ለመካፈል አስቡበት። ቤተሰቦች ለተቀበሉት "ለአገልግሎት የሚጠራ የጌታ ጥሪ" መልስ ሲሰጡ የነበራቸውን አጋጣሚዎች እንዲካፈሉ ጋብዟቸው።

## ወጣቶች

# በቤተመቅደስ ማገልገል

በቤንያም ኤ.

በአስራ ሰባት አመቴ፣ ስለወደፊት ህይወቴ ማሰብ ጀመርኩኝ፣ እናም ወደ ሚስዮን ለመሄድ እና ለመልከ ጼዴቅ ክህነት ለመዘጋጀት ምን ማድረግ እንደምችል ለማወቅ ወደ ሰማይ አባት ጸለይኩኝ። የጌታ ቤት ስለሆነና ከሰማይ አባቴ ጋር የምቀርብበት ስሜት እንዲሰማኝ የምችልበት ቦታ ስለሆነ ወደ ቤተመቅደስ በተደጋጋሚ መሄድ እንደሚገባኝ ተሰማኝ።

ስለዚህ 1 ሺህ ጥምቀቶች ለማከናወን አላማ ሰራሁ። ይህን አላማ ለመስራት እንደሚያስፈልገኝ ተሰምቶኝ ነበር፤ ይህን ማድረግ እንደሚያስፈልገኝ ለማወቅ ጾምኩኝ። የሰማይ አባታችን መልስ ሰጠኝ፣ እናም ወደ ተምፒኮ ሜክሲኮ ቤተመቅደስ በየሳምንቱ በቋሚ መሄድ ጀመርኩኝ።

500 ጥምቀቶች ከፈጸምኩኝ በኋላ፣ የቅድመ አያቶቼን ታሪክ ለመፈለግ አላማ አደረኩኝ፣ እናም ታሪኩን መፈለግ በጣም አስደስቶኝ ስሞችን በመፈለግ ለመተኛት አልቻልኩም ነበር። 50 ስሞች እና የቤተሰቤን ስምንት ትውልድ ታሪኮችን አገኘሁ፤ ለሁሉም የቤተመቅደስ ስራቸውን ፈጸምኩላቸው።

1 ሺህ 300 ጥምቀቶችን አከናወንኩኝ፣ እናም ከስምነሪ ተመረቅኩኝ፣ የመልከ ጼደቅ ክህነትን ተቀበልኩኝ፣ እናም አሁን በህይወቴ ታላቅ አላማዬ አንድ የነበረውን በሙሉ ጊዜ በሚስዮን እያገለገልኩኝ ነው ያለሁት።

## ልጆች

# ለሌሎች አንድ ነገር ለማድረግ እችላለሁ

እያንዳንዳችን ሌሎችን ለመርዳት አንድ ነገር ለማድረግ እን ችላለን። ፕሬዘደንት ሞንሰን ሁሉንም ማፍቀር እና እነርሱን እንዴት ለመርዳት እንደምንችል ለማወቅ ለመማር እንደሚገባን አስተምረዋል።

ከቤተሰብ ጋር እራት አብራችሁ ስትበሉ፣ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባላት በእዚያ ቀን ሌላን ለማገልገል ለማድረግ የሚችሉትን አንድ ነገር እንዲካፈሉ ሀሳብ አቅርቡ። እናንተ የነበራችሁን አጋጣሚ በማስታወሻችሁ ላይ በየወኑ ጻፉ።

© 2012 በIntellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፣ 6/11 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፣ 6/11 (እ.አ.አ) *First Presidency Message, August 2012* (እ.አ.አ) ትርጉም። Amharic። 10368 506

# እርዳታ በሚያስፈልግበት ጊዜ አንድ ነገር ለማድረግ መገኘት

*ይህን መዝገብ አጥኑ እና ተገቢ ከሆነ ከምትጎበኟቸው እህቶች ጋር ተወያዩት። እህቶቻችሁን ለማጠናከር እና የሴቶች መረዳጃ ማህበርን የህይወታችሁ ተሳታፊ ክፍል እንዲሆን እንዲረዳችሁ ጥያቄዎቹን ተጠቀሙባቸው።*

እምነት, ቤተሰብ, እርዳታ

እንደ ሴቶች የቤት ለቤት አስተማሪዎች፣ ከአላማዎቻችን አንዱ ቤተሰቦችን እና ቤቶችን ለማጠናከር ለመርዳት ነው። የምንጎበኛቸው እህቶች "ችግር ካለኝ፣ የሴቶች የቤት ለቤት አስተማሪዬ ሳይጠየቁ ይረዱኛል" ለማለት መቻል ይገባታል። ለማገልገል፣ የምንጎበኛቸው ሴቶች ምን እንደሚፈልጉ የማወቅ ሀላፊነት አለን። መነሳሳትን ስንፈልግ፣ እንድንጎበኝ የተመደብናት የእያንዳንዷ እህት መንፈሳዊ እና ስጋዊ ፍላጎትን እንዴት ለማሟላት እንደምንችል እናውቃለን። ከእዚያም ጊዜአችንን፣ ችሎታችንን፣ የእምነት ጸሎታችንን፣ እና መንፈሳዊና ስሜታዊ ድገፋችንን በመጠቀም በህመም፣ በሞት፣ እና በሌሎች ልዩ ጉዳዮች ጊዜ የርህራሄ አገልግሎቶችን ለመስጠት ለመርዳት እንችላለን፡[1]

ከሴቶች የቤት ለቤት አስተማሪዎች ሀተታዎች በኩል፣ የሴቶች መረዳጃ ማህበር አመራር በህመም፣ በአደጋ፣ ልጅ በመውለድ፣ በሞት፣ በአካለ ስንኩልነት፣ ወይም በሌሎች ችግሮች ምክንያት ልዩ የእርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ለማወቅ ይችላሉ። ከእዚያም የሴቶች መረዳጃ ማህበር ፕሬዘደንት የምታውቀውን ለኤጲስ ቆጶስ ትነግራለች። በእርሱም አበራር፣ እርዳታ የሚሰጠውን ታቀናጃለች።[2]

እንደ ሴቶች የቤት ለቤት አስተማሪዎች "ለደስታችን እንዴት ታላቅ ምክንያት አለን" ምክንያቱም "ይህንን ታላቅ ስራም ለመፈፀም በእግዚአብሔር እጅ መሳሪያ መሆናችን፣ ይህ በእኛ ላይ የወረደው በረከት ነውና" (አልማ 26፥1፣ 3)።

## ከቅዱሳት መጻህፍት

ማቴዎስ 22፥37–40፤ ሉቃስ 10፥29–37፤ አልማ 26፥1–4፤ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 82፥18–19

## ከታሪካችን

በቤተክርስቲያኗ የመጀመሪያ አመታት፣ የአባላት ቁጥር ትንሽ እና በአንድ ቦታ የሚገኙ ነበሩ። አባላት አንድ ሰው እርዳታ ሲያስፈልገው ወደኢያው እንዳታ ለመስጠት ይችሉ ነበር። ዛሬ የአባላታችን ቁጥር ከ 14 ሚልዮን በላይ ነው እናም በአለም ውስጥ የተበተንን ነን። የሴቶች የቤት ለቤት ጉብኝት ጌታ ልጆቹን ለመርዳት ያለው አላማ ክፍል ውስጥ ነው።

በቀዳሚ አመራር የመጀመሪያ አማካሪ የሆኑት ፕሬዘደንት ሔንሪ ቢ. አይሪንግ "በትልቋእና በተለያየ አለም ቦታ የምትገኝን ቤተክርስቲያንን ለመደገፍ እና ለማፅናናት የሚቻልበት ዘዴ ቢኖር እርዳታ በሚያስፈልጋቸው አጠገብ በሚገኙ በግለሰብ አገልጋዮች በኩል ነው" ብለዋል።

ቀጥለውም፣ "... እያንዳንዱ ኤጲስ ቆጶስ እና እያንዳንዱ የቅርንጫፍ ፕሬዘደንት የሚደገፍበት የሴቶች መረዳጃ ማህበር ፕሬዘደንት አለው" ብለዋል። "እርሷም የእያንዳንዷን እህት ፈተና እና ፍላጎት የሚያውቁ የሴት የቤት ለቤት አስተማሪዎች አሏት። በእነርሱም በኩል፣ የግለሰቦችን እና የቤተሰቦችን ሁኔታ ታውቃለች። እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ለመርዳት እና ግለሰቦችን እና ቤተሰቦችን ለመንከባከብ ኤጲስ ቆጶስ ያለውን ጥሪ ለማሟላትም ትረዳለች።"[3]

**ማስታወሻዎች**

1. *Handbook 2: Administering the Church* (2010)፣ 9.5.1፤ 9.6.2 ተመልከቱ።
2. *Handbook 2*፣ 9.6.2 ተመልከቱ።
3. ሔንሪ ቢ. አይሪንግ፣በ *Daughters in My Kingdom: The History and Work of Relief Society* ውስጥ (2011)፣ 110።

### *ምን ማድረግ እችላለሁ?*

1. ስጦታዬን እና ችሎታዬን ሌሎችን ለመባረክ እጠቀምበታለሁን?

2. የምጠብቃቸው እህቶች እርዳታ ሲያስፈልጋቸው እርዳታ ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆንኩኝ ያውቃሉ?

ለተጨማሪ መረጃ ወደ www.reliefsociety.lds.org ሂዱ።

© 2012 በIntellectual Reserve, Inc መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፤ 6/11 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፤ 6/11 (እ.አ.አ)
*Visiting Teaching Message, August* 2012 ትርጉም Amharic። 10368 506